## ተጨማሪ ይወቁ

የQR ኮዱን ይቃኙ፣ ከዚያም ተጨማሪ ሀብቶች እና አገናኞች ለማግኘት **ተደጋጋሚ ጥያቄዎች** የሚለውን አዝራር ይጫኑ።

Washington State Department of HEALTH

ይህንን ሰነድ በሌላ ቅርጸት ለመጠየቅ፣ ወደ 1-800-525-0127 ይደውሉ። መስማት የተሳናቸው ወይም የመስማት ችግር ያለባቸው ደንበኞች፣ እባክዎ ወደ 711 (Washington Relay) ይደውሉ ወይም በdoh.information@doh.wa.gov ኢሜይል ይላኩ።

ይህ የገንዘብ ድጋፍ የተገኘው ከUS Centers for Disease Control and Prevention (የአሜሪካ የበሽታ መቆጣጠሪያ እና መከላከያ ማዕከላት) ለWashington State Department of Health (ለዋሽንግተን ግዛት የጤና መምሪያ) (6NU50CK000515-05-14) በተሰጠ የገንዘብ ድጋፍ ነው።
**DOH 130-114 April 2026 Amharic**

ደንበኞች ስለ ክትባቶች ያዩትንና የሰሙትን የተሳሳተ መረጃ ይዘው ወደ እርስዎ ሊመጡ ይችላሉ።

**እውነታውን እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ ለመርዳት እነሆ።**

# የተሳሳተ መረጃ ማረም።



## ደንበኞቼ ሐሰተኛ የክትባት መረጃን እንዲለዩ እንዴት መርዳት እችላለሁ?

ደንበኞች በመስመር ላይ ወይም በማህበረሰባቸው ውስጥ አጠራጣሪ የሆነ ነገር ሲያዩ ወይም ሲሰሙ፣ እነዚህን ወሳኝ ጥያቄዎች እራሳቸውን እንዲጠይቁ ሊመክሩዋቸው ይችላሉ።

- **መረጃው ከየት የመጣ ነው?**
  ከሆስፒታል፣ ክሊኒክ ወይም የአካባቢ የጤና መምሪያ ከሆነ፣ እምነት የሚጣልበት ሊሆን ይችላል። እውነታውን ሳይገልጽ አስተያየት ከሚሰጥ ሰው የመጣ ከሆነ፣ ተጠራጣሪ ይሁኑ።
- **እንደ “ሁልጊዜ”፣ “በፍጹም” ወይም “በሙሉ” ያሉ ጽንፈኛ ቃላትን ይጠቀማል?** ለምሳሌ፦ “በፍፁም ክትባት አይወስዱም” ወይም “ሁሉም ክትባቶች በተመሳሳይ መንገድ ይሰራሉ።” የጤና መረጃ ብዙ ጊዜ እንደዚህ ቀላል አይደለም፣ እና እያንዳንዱ ክትባት የተለየ ነው።
- **እርስዎን ለማስፈራራት ወይም ለማስጨነቅ እየሞከረ ነው?**
  እንደ “ይህ እንዲያውቁት የማይፈልጉት ነገር ነው!” ወይም “አስደንጋጭ የሆኑ 10 የክትባት ምስጢሮች!” ባሉ ጥያቄዎች ይጀምራል? የሚያስፈራዎት፣ የሚያስጨንቅዎት ወይም የሚያናድድዎት ከሆነ፣ ሀሰተኛ ሊሆን ይችላል።
- **እውነታዎችን ሳያካፍል አንድን ታዋቂ ሰውን ወይም ድርጅትን ያጠቃል?**
  ለምሳሌ፦ “ዶክተሮች እየዋሹዎት ነው!” ወይም “መንግስት ስለ ክትባቶች እውነቱን እየሸፈነ ነው!” ከሆነ፣ ደግመው ያስቡበት።
- **የሆነ ነገር ለእርስዎ ለመሸጥ እየሞከረ ነው?**
  ምርቶችን ለማስተዋወቅ ብዙ ሀሰተኛ መረጃዎች ጥቅም ላይ ይውላሉ። በማንኛውም ጊዜ የሆነ ነገር እንድትገዙ የሚገፋፋዎት ከሆነ፣ እምነት የሚጣልበት ላይሆን ይችላል።

የQR ኮዱን ይቃኙ፣ ከዚያም የሚመከሩ የእውነታ ማረጋገጫ ድህረ ገጾችን እና ሌሎች የመረጃ ምንጮችን ለማግኘት ከ**የተሳሳተ መረጃ ሰነድ** ስር ያለውን አዝራር ጠቅ ያድርጉ።

